Piedmont HEALTHCARE

# ካልተጠበቀ የክፍያ ጥያቄ ለመጠበቅ ግልጽ ማስታወቂያ

## ካልተጠበቁ የህክምና ክፍያዎች ለመጠበቅ ያሉት መብቶችና የጥበቃ ከለላዎች

| |
|---|
| የአጣዳፊ ህክምና እርዳታ ቢያገኙ ፣ ወይም ከሕክምና ዋስትናዎ ጋር ባለውል በሆነ ሆስፒታል ወይም ውሎ ገብ የቀዶጥገና ማዕከል ውስጥ፤ በውልየልሽ ባለሙያ የህክምና አገልግሎት ቢያገኙ ከቀሪ ሂሳብ ነፃ ነዎት። በእንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች፤ በዋስትናዎ ከሚጠበቅቦት ድርሻዊ ቋሚ ክፍያ፣ ድርሻዊ ስሌት ክፍያ፣ እና/ወይም ቅድመ ክፍያ በላይ ሊጠየቁ አይገባዎትም። |

**<u>"ቀሪ ሂሳብ" (አንዳንዴም "ያልተጠበቀ ሂሳብ" ተብሎ የሚጠራው) ምንድነው?</u>**

ሓኪም ወይም ሌላ የጤና ባለሞያ ሲያዩ፤ <u>ከኪስዎ የሚከፍሏቸው ወጪዎች</u> ሊገጥሞት ይችላል ፤ እንደ <u>ድርሻዊ ቋሚ ክፍያ</u>፣ <u>ድርሻዊ ስሌት ክፍያ</u>፣ ወይም <u>ቅድመ ክፍያ</u> የመሳሰሉትት። ከሕክምና ዋስትናዎ ጋር ውል የሌለው የጤና ባለሙያ ወይም ተቋም ቢያዩ፤ ተጨማሪ ወጪዎችን ወይም ሙሉውን ሂሳብ መክፈል ይኖርቦት ይሆናል።

"ውልየለሽ " ማለት ጤና ባለሞያዎቹ ወይም ተቋሞቹ ከሕክምና ዋስትናዎ ጋር የአገልግሎት ውል አልተፈራረሙም ማለት ነው። ውልየለሽ ጤና ባለሞያዎች ፤ የሕክምና ዋስትናዎ ለተባለው አገልግሎት በሚከፍለውና እነሱ በሚጠይቁት መሀል ያለውን የክፍያ ልዩነት ሊጠይቁ የሚፈቀድላቸው ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ይኼ **"ቀሪ ሂሳብ"** ይባላል። ይኼ ክፍያ፤ ለባለውል ፣ ለተመሳሳይ አገልግሎት ከሚከፈለው የበለጠ ሊሆን ከመቻሉም ሌላ በጤና ዋስትና ስምምነትዎ ከሚጠበቅብዎ የቅድመ ክፍያ ግዴታዎ ወይም ለአመታዊ ከኪስ ወጪ ጣርያ ማሟያነት ላይታሰብሎት ይችላል።

"ያልተጠበቀ ሂሳብ" ያላሰብነው ቀሪ ሂሳብ ነው። እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሊደርስ የሚችለው ማን እንደሚንከባከበን መወሰን ባልቻልንባቸው አጋጣሚዎች ሲሆን፤ እንደ ምሳሌም አጣዳፊ የህክምና ዕርዳታ አስፈልጎት ወይም ከባለውል የህክምና ተቋም ጋር ቀጠሮ ይዘው ሄደው ግን ሳያውቁት በውልየለሽ ባለሙያ ቢታከሙ የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል። ያልተጠበቁ የህክምና ወጪዎች ፣ እንደተሰራው ስራና አገልግሎት መጠን፣ ብዙ ሺ ዶላርም ሊያወጡ ይችላሉ።

**<u>የሚከተሉት ሁኔታዎች ቢገጥሙዎት ከቀሪ ሂሳብ ሀላፊነት ተጠብቀዋል</u>**

### አጣዳፊ የህክምና እርዳታ አገልግሎቶች

አጣዳፊ የጤና ችግር ቢገጥሞትና፤ በውልየለሽ የጤና ባለሞያ ወይም ተቋም አስቸኳይ አገልግሎት ቢያገኙ፤ ክፍያ ሊጠየቁበት የሚችሉት ቢበዛ በዋስትናዎ መሰረት ለባለውል የሚከፍሉትን የክፍያ ድርሻዎን ብቻ ነው (ለምሳሌም ድርሻዊ ቋሚ ክፍያዎን፣ ድርሻዊ ስሌት ክፍያዎን እና ቅድመ ክፍያዎን)። የእነዚህን አጣዳፊ እርዳታ አገልግሎቶች ቀሪ ሂሳብ ሊጠየቁባቸው አይችሉም። በጽሁፍ መስማማትዎንና በቀሪ ሂሳብ እንዳይጠየቁ ከለላዎን ካላነሱ በስተቀር፤ ከአጣዳፊ የህክምና እርዳታውም በኋላ ያሉት ማረጋግያ አገልግሎቶች በዚሁ ስር ይጠቃለላሉ።

### በባለውል ሆስፒታል ወይም ውሎገብ የቀዶጥገና ማዕከል የሚሰጡ አንዳንድ አገልግሎቶች

ባለውል በሆነ ሆስፒታል ወይም ውሎገብ የቀዶጥገና ማዕከል አገልግሎት ሲያገኙ፤ እዛ ከሚንከባከቦት ባለሙያዎችአንዳንዶቹ ውልየለሽ ሊሆኑ ይችላሉ። በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች፤ እነዚህ አገልግሎት ሰጭዎች ክፍያ ሊጠይቁ የሚችሉት በዛ ቢባል በጤና ዋስትናዎ ስር የውሎ የክፍያ ድርሻዎን መጠን ብቻ ነው። ይህ የአጣዳፊ ህክምናን፣ የማደንዘዣ አገልግሎትን፣ የናሙና ጥናትን፣ የምስላዊ ምርመራን፣ የላቦራቶሪ ምርመራን፣ የአራስ ልጅ ህክምናን፣ የቀዶ ጠጋኝ ረዳትን አገልግሎት፣ የአልጋ ህሙማን ወይም የርብርብ ህክምና ባለሞያ አገልግሎቶችንም ያጠቃልላል። እነዚህ ባለሙያዎች የቀሪ ሂሳብ ክፍያ ሊልኩቦት አይችሉም፤ በቀሪ ሂሳብ እንዳይጠየቁ የከለላ መብቶቾንም እንዲያነሱ ሊጠይቁዎት አይችሉም።

በእነዚህ ባለውል ተቋሞች ውስጥ ሌሎች አይነት አገልግሎቶችን ቢያገኙ፤ ጽሁፋዊ ፈቃድዎን ካልሰጡና የከለላ መብቶችን ካላነሱ በስተቀር፣ ውልየለሽ ባለሙያዎቹ የቀሪ ሂሳብ ክፍያ ሊልኩቦት አይችሉም።

መቼም ቢሆን፣ በቀሪ ሂሳብ ላለመጠየቅ የከለላ መብትዎን እንዲያነሱ ሊገደዱ አይችሉም። ከውልየለሽ አገልግሎት ሰጪዎችም የጤና እንክብካቤ የመቀበል ግዴታ የለቦትም። በህክምና ዋስትናዎ መረብ ውስጥ የታቀፈ ባለሙያም ይሁን የጤና ተቋም መምረጥ ይችላሉ።

<u>**በቀሪ ሂሳብ መጠየቅ በማይቻልበት ሁኔታ፤ የሚከተሉትም ከለላዎች አለዎት ።**</u>

- የእርሶ ብቸኛ ሀላፊነት ከህክምና ወጪው የራስዎን ድርሻ ብቻ (ልክ በባለውል ባለሙያ ወይም ተቋም ቢታዩ የሚከፍሏቸውን እንደ ድርሻዊ ቋሚ ክፍያዎን፣ ድርሻዊ ስሌት ክፍያዎን እና ቅድመ ክፍያዎን) መክፈል ነው። ተጨማሪ ወጪዎች ቢኖሩ የህክምና ዋስትናዎ ለውልየለሽ ባለሙያዎቹና ተቋሞቹ በቀጥታ ይከፍላቸዋል።

- በአጠቃላይ ሲታይ የህክምና ዋስትናዎ
  - አጣዳፊ የህክምና እርዳታ አገልግሎቶችን በሚመለከት፤ አገልግሎቶቹን ለማግኘት ፈቃድ ማስወጣት ሳይጠበቅቦት (በሌላ ስሙ ቅድሚያ ፈቃድ)፤ የመክፈል ግዴታ አለበት ።
  - በውልየለሽ ባለሙያዎች የሚደረጉ የአጣዳፊ እርዳታ አገልግሎቶችን የመክፈል ግዴታ አለበት ።
  - ለአገለገሎት ባለሙያ ወይም ተቋም ከእርሶ የሚጠበቅቦትን የክፍያ ድርሻ፤ ልክ ለባለውል ባለሞያ ወይም የጤና ተቋም ከሚከፍለው አንጻር ማስላትና፤ ይህንኑም መጠን በሕክምና ወጪ ማብራርያ ውስጥ ማሳየት አለበት ።
  - ለአጣዳፊ እርዳታ አገልግሎት ወይም በውልየለሽ ለተሰጡ አገልግሎቶች የሚከፍሉትን ማንኛውንም ወጪ፤ ለባለውል ቅድመ ክፍያ ግዴታዎ እና ከኪስ ወጪ ጣርያዎ ማሟያ እንዲውልሎ ማድረግ አለበት።

**አላግባብ ክፍያ ተጠይቄያለሁ ብለው ካሰቡ ፡**

ለመረጃ እና ለአቤቱታዎች የፌዴራል ስልክ ቁጥር እነሆ- 1-800-985-3059

በፌዴራል ህግ ስር ስላልዎት መብቶች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የሚከተለውን ድረገፅ ይጎብኙ ፡፡
www.cms.gov/nosurprises/consumers

ለመረጃና አቤቱታዎች- የጆርጅያ ሆሰፒታሎች ማህበር (GA Hospital Association-GHA) ስልክ ቁጥር እነሆ- 1-800-985-3059

በጆርጅያ የተወካዮች ም/ቤት ሕግ 888 ስር ስላሎት መብቶች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ https://www.gha.org/Advocacy/Health-Care-Finance ድረገጽን ይጎብኙ ።